በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

የተሰጠ መግለጫ

ነሐሴ 3ቀን 2007ዓም

## ወያኔ ፍርድ መገምደል ፍትህን መግደል ልማዱ ነው።

ወያኔ/ኢህአዴግ ገና ከመነሻው ለስርዓቱ ሎሌ ሆነዉ ኢያገለግሉም ያላቸውን ድርጅቶች፣ ማህበራት፣ ግለሰቦችም ሳይቀር በሐሰት እየከሰሰ ፣ የሐሰት ምስክር  እያሰለጠነ ፣ የውሸት መረጃ እያዘጋጀ ፣ በአምሳሉ በፈጠረው ፍርድ ቤት ተብዬ የካድሬዎች ስብስብ እያቀረበ ወህኒ እንዳወረዳቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነዉ። ዳኞቹም ሲመለመሉና ሲሰለጥኑ ሕግን በሕግነቱ ለመተርጎም ፣ የዜጎች መብት እንዳይጣስና ፍትህ እንዲሰፍን ሳይሆን የገዢዎችን ትዕዛዝ ለማስፈጸም የሚቀመጡ እንደሆነ በ24 ዓመታት የተስተዋለ ነዉ።

የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ዓለም  ኣቀፍ  የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎችንና እንዲሁም አገሪቱ ትመራበታለች ተብሎ በተቀረጸው ሕገ መንግስት የተካተተዉን በነጻ የመደራጀት መብቶች ሕግ መሰረት በማድረግ ሲንቀሳቀሱ ወያኔ የራሱን ካድሬዎች አሰባስቦ አመራሩ ላይ በማስቀመጥ ማህበሩን ለማፍረስ ወሰነ።ያኔም እንዳሁኑ ኣይን ያወጣ የፍትህ መጓደል ባይታይም ኢመማን ለማፍረስ ፍ/ቤቶችን ሊጠቀምባቸዉ ባጅቷል። ለሕሊናቸው ይሠሩ የነበሩ አንዳንድ ዳኞች በመኖራቸው አራት ጊዜ ለኢመማ ተፈርዶ አስፈጻሚው አካል የፖለቲካ ክንፍ በመሆኑ ውሳኔው መና ሆኖ ቀርቷል።በኢትዮጵያ መምህራን ፣ በኢመማ አመራር አባላት ላይ የደረሰውን ወከባ፣ እስራት፣ ማሰቃየት፣ ግድያና ስደት የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያውቀው ነዉ።ለመብት ማስከበር የሚታገል ሁሉ የወያኔ ሰለባ ይሆናል። በኢትዮጵያ ከወያኔ/ኢህአዴግ ውጪ በፖለቲካ ድርጅት መሳተፍ ፣ በሙያ ማህበር መሰባሰብ ፣ የአምነት ተቋማትን ማቋቋምና መሪዎችን በነፃነት መምረጥ በወያኔ ቁጥጥር ስር በሚሰጠው መመሪያ መሰረት የፓርቲ ክንፍ ሆኖ ካልሠራ በተጠመደ ፈንጂ ላይ እንደ መራመድ ነዉ የሚቆጠረው።

“ የሙስሊሙ ማህበረሰብ የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ” ከስያሜዉ  ለመረዳት እንደሚቻለውና በሰላማዊ ትግሉ እንደታየዉ የአህባሽ አስተምህሮ ከሙስሊሙ ህብተረሰብ ፍላጎት ውጪ በግዳጅ ሊጫን እንደማይገባ፣ መጅሊስ በሚል የሚጠራው የሙስሊሞች የዕምነት ድርጅት በአማኞቹ በሚመረጡ እንዲመራ፣ የዕምነትና የመደራጀት መብታቸዉ እንዲከበር ፣መንግሥት በሚመለከተዉ ደረጃ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ለማገዝ ከህዝቡ መካከል ተመርጠዉ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር እንዲወያዩና መፍትሔ እንዲገኝ ነዉ  የተዋቀረው፤ ተልእኮውም ይኸው ነው። ለዚህም ሟች ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ጨምሮ የፌዴራል ጉዳዩች ሚኒስቴር መ/ቤትና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር እየተወያዩ ፣ ጥያቄዎች እያቀረቡ፣በውይይቱ የተደረሰባቸውን ጉዳዮች  ለሕዝቡ በማሳወቅ ሂደት ላይ ነበሩ።በሂደቱ ወያኔ የውይይቱንና መፍትሔ የመፈለጉን አካሄድ ሰርዞ የፖለቲካ ሸር መሸረቡን ተያያዘው። ምን ጊዜም የሕዝብ ድምፅ ለመስማትና ለማክበር ፍላጎት የሌለው ወያኔ የመብት ጥያቄ ይዘው የቀረቡትን “የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ” አባላትን በሐሰት ወንጅሎ የሙስሊሙን ማህበረሰብ ጥያቄ የማፈን ተግባሩን በእቅድና በፕላን አራመደ።ለዚህ ደግሞ ቀደም ሲል በሕግ ስም ለመብታቸዉ የሚታገሉ ንፁሐን ዜጎች መቅጫ ሆኖ የተዘጋጀው የሽብርተኛ አንቀጽ እየተመዘዘ መከሰስ፣ አባይ ምስክር ማሰልጠን፣የሐሰት ማስረጃ ማቀናበር ነው የሚጠበቀው። “አኬልዳማ” እና “ሐረካ” ንም ያስታውሷል። በሕዝብ መካከልም ውዥንብር ለመፍጠር ብዙ ተሰርቷል።ይህ እንዳለ ሆኖ

- የብዙሃኑ ጥያቄ አደባባይ ወጥቶ በመፈክር ታጅቦ ሕዝብ አይቶታል፣ ሰምቶታል።
- ከምእመናን የቀረቡ ጥያቄዎችን ኮሚቴው ይዞ ቀርቦ የወያኔን መንግሥት ከሚወክሉ አካላት ጋር ተወያይቷል።
- የተካሄዱ ውይይቶች፣ የቀረቡ ጥያቄዎች በድምፅና በምስል ተቀርጸዋል።
- በመገናኛ ብዙሃን በይፋ የተላለፉም ነበሩ።ይህና የመሳሰሉት ሰላማዊ እንቅስቃሴዎች ሲገመገሙ ወደ ሽብርተኛ ጓዳ የወሸቃቸው አንዳች ነገር ኣልታየም።ነገሩ ኢያጅቦ ኢታዳፍርሽብኝ እንዳለውና የግድ ነገር ፍለጋ ካልሆነ በቀር። ይልቁንስ ሐራምቦ ቆቦ የረገጠውና በሀሰት ፈጠረ የተገጣጠመው የሽብርተኝነት ውንጀላ የመብት ጥያቄ ባነሱና ለፍትህ በቆሙ ወገኖች ላይ የሚፈጸም የሐሰት ክስና የተውኔት ገቢር ተከታታይ እንደሆነ አጉልቶ እያሳየ ነው።

P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

*ከዚህ አንጻር በአገራችን በሕግ መተዳደርና ፍትህ ማግኘት አለ ብሎ መናገር ከማይቻልበት ደረጃ ደርሰናል። እንዲያዉም አንዳንድ ምሁራን የወያኔ /ኢህአዴግን ሕገ መንግሥት " ሕገ አራዊት" በሚል ሲጠሩ ተሰምቷል።ተግባሩም ያረጋገጠዉ ይኸንኑ ነው። ፍትህ ብዙን ጊዜ ነጠላውን አይነገርም። ቀጥተኘነቱን፣ ትክክለኛነቱን ፤የማይዛነፍ መሆኑን ለመግለጽ ሲባል "ዕርትህ ፍትህ" ነዉ የሚባለው።የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲታገልለት የነበረውና የ1966ቱን አብዮት ያመጣው ዕርትህ ፍትህ እንዲሰፍን ነበር።እንደ ወያኔ በፍትህ ያላገጠ ፣ መብቶችን የረገጠ፣ በአገር ሉዓላዊነትና በሕዝብ አንድነት ላይ አደገኛ ጥያቄ ያስቀመጠ ሥርዓት የለም። በሙስሊሙ ሕብረተሰብ የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ላይ ሰኞ ሐምሌ 27 ቀን 2007 ዓ.ም የወያኔ የይስሙላ ፍ/ቤት ከ7- 22 ዓመታት የእስር የፖለቲካ ውሳኔ በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ በጥብቅ ያወግዛል። መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ ባጠቃላይ ሕብረተሰቡ ፍትህ የሰፈነባት፣ ዳር ድንበሯ የተከበረባት፣ ዜጎች ሰዉ በመሆናቸው ብቻ የሚከበሩባት አገር እንድትገነባ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት በጋራ እንዲታገሉ ጥሪውን ያቀርባል።*

*ሕግና ሥርዓት እንዲከበር እንታገል!!*
*"ፍትህ አይጓደል-ሕዝብ አይበደል" ምላሽ ያላገኘ መፈክር ነው!!*